ADDIS KETEMA SUB – CITY EDUCATION OFFICE

SECOND SEMESTER AMHARIC FINAL MODEL EXMINATION

FOR ALL GRADE 8 (EIGHT) STUDENTS

SENE 2012/ JUNE 2020

TIME ALLOWED 1:00

NUMBER OF ITEMS: 60

GENERAL DIRECTIONS

ATTEMPT ALL THE **60 ITEMS** CONTAINED IN THE EXAMINATION PPER. FOR EACH ITEM, FOUR SUGGESTED OPTIONS ARE GIVEN. AMONG WHICH ONLY ONE IS THE CORRECT ANSWER, SO CHOOSE THE CORRECT ANSWER FROM THE SUGGESTED OPTION AND BLANCKEN THE LETER OF YOUR CHOICE IN THE ANSWER SHEET.

TIME ALLOWED TO WORK TO THIS EXAM **1:00** WHEN TIME IS OVER YOU MUST IMMEDIATELY STOP WORKING, LAY YOUR PENCIL DOWN AND REMAIN SIT TILL ALL ANSWER SHEETS COLLECT AND THE INVIGILATOR TELLS YOU TO LEAVE THE EXAMINATION ROOM.

ANY FORM OF CHEATING OR AN ATTEMPT TO CHEAT IN THE EXAMINETION ROOM IS SUBJECTED TO FORMALITY.

DO NOT TURN THIS PAGE TILL YOU ARE TOLD TO DO SO!

አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ት/ጽ/ቤት የ 2012 ዓ. ም ለ 8 ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሞዴል ፈተና

ስም----------ክፍል------ተ.ቁ------የተፈቀደው ጊዜ 60'

<u>መመሪያአንድ፦</u> ቀጥሎ ከ 1 እስከ 54 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል ።ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።

1) ጎበዝ ተማሪ የመምህሩን ክብር ይጠብቃል በሚለው ዐ.ነገር የስም ገላጩ _ነው።

A.ተማሪ B. ጎበዝ C. ይጠብቃል D. ክብር

2) መሠረት ከፋኛ ታመመች። በሚለው ዐ.ነገር ተውሳከግሱ የትኛው ነው?

A. መሠረት B.ከፋኛ C.ታመመች D. ከፋኛታመመች

3) ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ትክክለኛ የምዕላድ አተናተን ሥርዓት የሚታይበት የቱ ነው?

A. የ-ወንድሞቼ-ን B. ስለ-መለከታዊ-ነት-ኡ C. በግ-ኦች-አችን D .የቤተሰብ-ኦች-ኡ

4) "መጽሐፌን" በሚለው ቃል ውስጥ ያለው ባለንብረትነትን አመልካች ቅጥያ_____ነው።

A. -ፌ B.- ኤ C .-ን D .-ፌን

5) ከሚከተሉት ቃላት መካከል 3 ኛ መደብ፣ነጠላ ቁጥር፣አንስታይ ፆታ የሚያመለክተው የቱ ነው?

A. ሰበረ B. ሄደች C. አለፉ D .ጻፍን

6) "አስተማሪች" በሚለው ቃል ውስጥ ያለው ፆታ አመልካች ቅጥያ_____ነው።

A. አስ- B. ኧ- C .-ኧች D. -ች

7) ረዘመ ብለን ረጅም ካልን አታለለ ብለን_____እንላለን።

A. ማታለል B. አታላይ C. አታለለች D. አታላይነት

8) ከሚከተሉት አማራጮች መካከል አንዱ የክርክር አዘገጃጀት ና አቀራረብ መመሪያ አይደለም።

A. መረጃዎችን መሰብሰብ B. ትኩረትን በተናጋሪው ሰብዕና ላይ ማድረግ C .ርዕስ መምረጥ D. ተገቢነት ያላቸውን ቃላት መጠቀም

9) "የተሸለመዉ ልጅ ንግግር አደረገ"። በሚለው ዐ.ነገር ስማዊ ሐረጉ_____ነው።

A. ንግግር አደረገ B. ልጅ ንግግር አደረገ C. የተሸለመው ልጅ D. ንግግር

10) ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የድርሰት አካል ያልሆነው የቱ ነው?

A. መግቢያ B. ንዕዕር C. ሐተታ D. መደምደሚያ

11) ከሚከተሉት አማራጮች መካከል አንዱ የቃለጉባኤ አያያዝ መመሪያ አይደለም።

A. ቀን፣ሰዓትና ቦታ መጻፍ B. የግል አስተያየትን ማካተት C. አጀንዳዎችን መጻፍ

D. የውሳኔ ሐሳብ መስጠት

12) ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የሥነ ቃል ዘውግ ያልሆነው የቱ ነው?

A. ፉከራ B. ተረት C. ተውኔት D. እንቆቅልሽ

13) ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ልዩ የሆነው የቱ ነው?

A. ያልጠረጠረ ተመነጠረ B. እመትቀበጢና መቀነቷ መቶ ከዘጠና

D. ድር ቢያብር አንበሳያስር

14) ቃል ኪዳን የፈጠራ ሥራዎችን ማንበብ ትወዳለች።በመሆኑም "ይርቶጋዳ" የተሰኘውን ልቦለድ አንብባ ታሪኩን ባጭሩ ለጓደኞቿ ብትነግራቸው ቃልኪዳን የተጠቀመችው የንባብ ዓይነት የትኛው ነው?

A. የዝግታ ንባብ B. የፍጥነት ንባብ C .የገረፍታንባብ D. የአሰሳንባብ

15) "ትመጫለሽ ብዬ ሳይ ማዶ ሳይ ማዶ

የልጅነት ዓይኔ ሚሚ እንደበረዶ" የሚለው ቃላዊ ግጥም ለየትኛው የምጣኔ ዓይነት ምሳሌ ይሆናል?

A.ቡሄ በሉ B. ሰንጎመገን C .የወል ቤት D. የዮሐንስ ቤት

16) ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የውስብስብ ዐ.ነገር ምሳሌ ያልሆነው የቱ ነው?

A.ሳሙኤል ስለረበሸ ተባረረ። C .መርከብምሳዋንበልታሂደች።

B. ኀበዝ ተማሪ የመምህሩን ክብር ይጠብቃል። D. ፌርማታው አጠገብ የቆመው ፖሊስ ሌባውን በርቀት አየው።

17) ናትናኤል ስዕል ሳለ። የሚለው ዐ.ነገር የተሟላ መልዕክት እንዲያስተላልፍ ማሰሪያ አንቀጹ እንዴት ሆኖ መነበብ አለበት?

A. ጠብቆ B.ላልቶ C. ረግቶ D. ሰልቶ

18) ቀጥሎ ከቀረቡት ዐ.ነገሮች መካከል የመሆን ግስን በመጠቀም የተመሠረተው የቱ ነው?

A.ባርኮት ብርጭቆ ሰበረ። C.ልኡል ኀበዝ ተማሪ ነው።

B.ማሕሌት የቤት ሥራዋን ሠራች። D.ሀና መጽሔት አነበበች።

19) የአንቀጽን ዋና ሐሳብ የያዘው ዐ.ነገር_____ይባላል።

A. አንጓ B. ኃይለቃል C. መዘርዝር D. ሁሉም

20) የግጥም አንድ መስመር ተሳክቶ ሲያበቃ የሚሰጠው ስያሜ_____ይባላል።

A. ቤት B. ስንኝ C. አርኬ D. አንጓ

21) በአንድ ትንፋሽ የሚነበብ የቀለማት ስብስብ_____ይባላል።

A. ቤት B. ስንኝ C.ሐረግ D. አንጓ

22) ልዩ የሆነው የቱ ነው?

A. ይህ B. እነዚያ C. ይህች D. እነዚህ

23) ከሚከተሉት ቃላት መካከል በውሰት ከጉራግኛ ወደ አማርኛ የገባው የቱ ነው?

A. ጨጨብሳ B. እንሰት C. ውሻ D.ጳጳስ

24) ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በፊደል ገበታ ሥርዓት ቀድሞ የሚገኘው የቱ ነው?

A. ዝናብ B. ደመና C .ዓለም D. ጭፍግ

25) የመንስኤና ውጤት ትስስር የሚታይበት የቱ ነው?

A.አቤል ንበዝ ተማሪ ነው። C. ስንታየሁ ከክፍል ተባረረ።

B.ትንሳኤ የፈጠራ ሥራዎችን ታነባለች። D. ያልጠረጠረ ተመነጠረ።

26) ትክክለኛ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም የሚታይበት ዐ.ነገር የቱ ነው?

A. ለሁሉም ጊዜ አለው አለ ጠቢቡ ሰለሞን። C."ለሁሉም ጊዜ አለው" አለ ጠቢቡ ሰለሞን።

B."ለሁሉም ጊዜ አለው አለ" ጠቢቡ ሰለሞን። D."ለሁሉም ጊዜ አለው"፤ አለ ጠቢቡ ሰለሞን።

27) "ሕይወት ያለው በድን" የሚለው አባባል የቀረበበት የዘይቤ ዓይነት_____ነው።

A. ንቡር ጠቃሽ ዘይቤ B. አያዎ ዘይቤ C. ምፀት ዘይቤ D. እንቶኔ ዘይቤ

28) የጠጅ አጣጣል ካልን የማር_____እንላለን።

A.አቆራረጥ B. አበላል C. አላላስ D. አወጣጥ

29) "ማርቀምሼ አላውቅም እኔ ወንድማችሁ

የሀገሬ ወጣቶች ተማሩ እባካችሁ" የሚለው ቅኔ ሕብረ ቃሉ_____ው።

A. ወንድማችሁ B. ቀምሼ C. ወጣቶች D.ተማሩ

30) ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ጥምር ቃል ያልሆነው የቱ ነው?

A. ቤተመጻሕፍት B. አየርመንገድ የአመጋገብ ሥርዓት D. ሆደመጋዝ

31) "ጥቁር ልብስ መልበስ በኢትዮጵያውያን ባሕል የሐዘን ምልክት ሲሆን በህንዳዊያን ደግሞ የደስታ ምልክት ነው" የሚለው ሐሳብ የየትኛው ዘይቤ ምሳሌ ይሆናል?

A.ግለሰባዊ ተምሳሌት B. ተለምዷዊ ተምሳሌት C.ዓለማቀፋዊ ተምሳሌት

D. በስመሀዳሪ ዘይቤ

32) ከሚከተሉት አማራጮች መካከል አፍራሽ መልዕክትን የያዘው ምሳሌያዊ አነጋገር የቱ ነው?

A.ሴት ወደ ማጀት ወንድ ወደ ችሎት C. የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል

B.ሳይቃጠል በቅጠል D. ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ

33) ልጨኛ ሲል _____ማለቱ ነው።

A. ቁምነገረኛ B. ተንኮለኛ C. ክልፍልፍ D. አብግን

34) ደመኛ ለሚለው ቃል ተቃራኒው ነው።

A. ጠላት B.ወዳጅ C. ባላንጣ D. ጎረቤት

35) የደብዳቤ አጻጻፍ ካልን የቃለጉባኤ_____እንላለን።

A. አካሄድ B. አደረጃጀት C. አያያዝ D. አጻጻፍ

36) የአጭር ልቦለድ ባሕርይ ያልሆነው የቱ ነው?

A. ቁጥብነት B. ጥድፊያ C. ነጠላ ውጤት D. ሰፊ የመቼት ገለጻ

37) ሳምራዊት መጽሐፍ ገዛች። በሚለው ዐ.ነገር ያለው ግስ ዓይነቱ ነው።

A. ተሻጋሪ ግስ B .ኢ-ተሻጋሪ ግስ C. የመሆን ግስ D. ኢ-ሳቢ ግስ

38) ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የመስተዋድዳዊ ሐረግ ምሳሌ የሆነው የቱ ነው?

A. የዶሮ ወጥ B. ወደ ጎንደር C. የአንገት ሐብል D. ጎበዝ ተማሪ

39) የተውኔት ዋና ክፍል_____ይባላል።

A. ትዕይንት B. ፋርስ C. ገቢር D. ኮሜዲ

40) በገጸ ባሕርያት መካከል የሚከሰተው ግጭት እየከረረ (እየተፋፋመ) ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ _____ይባላል።

A. ፍልሚያ B. ልቀት C. መንስኤ ግጭት D.ጡዘት

41) የተውኔት ደራሲ_____ይባላል።

A. ሐያሲ B. አርታኢ C. ጸሐፌ ተውኔት D. መራሔተውኔት

42) የድርሰት ዋና ሐሳብ የሚቀርብበት ክፍል__ይባላል።

A. መግቢያ B. መደምደሚያ C. ሐተታ D .ማጠቃለያ

43) ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የሰዋሰው ስሕተት የማይታይበት የቱ ነው?

A. ሊቃውንቶች B. መምህራኖች C. አዕዋፍ D. አዕዋፋት

44) በጎጃም የተወለዱት አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ ጥሩ ደራሲ ነበሩ። በ 1948 ዓ.ም "ተረትተረት"ን፣በ 1958 ዓ.ም "ፍቅር እስከመቃብር"ን፣በ 1974 ዓ.ም "ወንጀለኛው ዳኛ"ን እና በ 1980 ዓ.ም "የእልምዣት"ን ጽፈው ለአንባቢያን

አቅርበዋል። ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ባበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከአዲስ አበባዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ተቀብለው በ 1995 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።ይህ ጽሑፍ ለየትኛው የድርሰት ዓይነት ምሳሌ ይሆናል?

A. ገላጭ ድርሰት B. ስዕላዊ ድርሰት C. ተራኪ ድርሰት D. አመዛዛኝ ድርሰት

45) "እነዚህን ወንበሮችና እነዚያን ጠረጴዛዎች ቶሎ ቶሎ አጽዷቸው።" በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ ያለው የሩቅ ጠቋሚ መስተአምር_____ነው።

A. እነዚህ B. እና C .እነዚያ D. እነዚህ ና እነዚያ

46) "ዕውቀታችሁን" ከሚለው ቃል ጋር በቅርፅ የሚመሳሰለው የቱ ነው?

A. ቅጥያዎቻችሁን B. የችሎታችሁን C. ድርሰታችሁን D. ቀልዶቻችሁን

47) ዛሬ ቁንጅና ሳሎን ሄጄ ሹሩባ ተሰተካክዬ መጣሁ። በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ በስሕተት የገባው ቃል የትኛው ነው?

A. ቁንጅና B. ሳሎን C. ተሰተካክዬ D. መጣሁ

48) ሐረግ መዘዘ ሲል____ማለቱ ነው።

A. ታሪክ አቀረበ B. ሕግ ገባ C .ዘርቆጠረ D. ሰበብአበዛ

49) "ዝግ" የሚለው ቃል ጠብቆ የሚነበበው በየትኛው ዐ.ነገር ውስጥ ነው?

A. በሩ ዝግነው። B. ኮሚቴው ዝግ ስብሰባ አካሄደ።

C. ዝግ ብለሽ ሂጂ። D. ልጅቱ ዝግ ናት፤አትናገርም።

50) ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ከሌሎች ጋር በፍቺ የማይመሳሰለው ቃል የትኛው ነው?

A. ተቀበተተ B. ተነፋ C. ተነፈገ D. አበጠ

51) የንግግር ችሎታን አዳብሮ ሰዎችን ለማሳመን በየትኞቹ በቂ ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል?

A. ጭውውት፣ውይይት፣ክርክር C. ትረካ፣ሙግት፣ድራማ

B. ሪፖርት፣ጥናት፣ጽሕፈት D. ንባብ፣ምርምር፣ሒስ

52) ከቋንቋ ክሂሎች መካከል ቀዳማይ ዘርፍ የሆነው የቱ ነው?

A.መናገር B. ማዳመጥ C. መጻፍ D. ማንበብ

53) የድመት ልጅ ሙቄሊት ከተባለ የዝሆን ልጅ_____ይባላል።

A. ደቦል B. ግልገል C. ኤልሞሌ D. ጥጃ

54) ግጥም አንጓ እንዳለው ሁሉ ዝርው ጽሑፍም_____አለው።

A. ድርሰት B. ዐ.ነገር C. ሐረግ D. አንቀጽ

<u>መመሪያሁለት፦</u> ከጥያቄ 55 እስከ 60 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ግጥም ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ግጥሙን በጥሞና ካነበባችሁ በኃላ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ተገቢውን መልስምረጡ።

ተነሱ እባካችሁ ስለዚህ ድከሙ

ሊቃውንት በመጽሐፍ የሚሉትን ስሙ

ትጉ ሥሩ ልፉ ለስልጣኔ አስቡ

ጥበብን ፈልጉ መጽሐፍን እንብቡ

መጽሐፍን አንብቡ ከሁሉም ይልቅ

ቢቀዳ ቢቀዳ ጥቅሙ የማያልቅ

መጽሐፍ ቃልኪዳን ነው ሁሉን የሚያለማ

ሰውን የሚያፋቅር ሕዝብን የሚያስማማ

ይገባል ስለዚህ ለማግኘት ጥበብ

በያይነቱ መጽሐፍ ተጽፎ ለሕዝብ

ትርጉሙን ማጠጣት ቃሉን መመገብ

(ከበደሚካኤል።1994 ዓ.ም። የቅኔውበት ።።አ.አ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ ገጽ ፴፯ ለፈተና እንዲያመች ተደርጎ የተወሰደ)

55) በግጥሙ ውስጥ ስንት ስንኞች አሉ?

A. 11 B. 22 C. 6 D. 5

56) የግጥሙ አራተኛ ስንኝ መነሻ ሐረግ ከሚከተሉት የትኛው ነው?

A. መጽሐፍን አንብቡ B. ጥበብን ፈልጉ C. ከሁሉም ይልቅ D. ቢቀዳ ቢቀዳ

57) የግጥሙ ደራሲ በግጥሙ ውስጥ ጥበብን ለመግለጽ በዋናነት የተጠቀመበት ቃል የትኛው ነው?

A. ሊቃውንት B. ቃልኪዳን C. መጽሐፍ D. ሰው

58) በግጥሙ ውስጥ በሳድስ የሚጨርሱ ስንኞች ብዛት ስንት ነው?

A.4 B. 2 C. 11 D.5

59) ግጥሙ የተሟላ መልዕክትን እንዲያስተላልፍ የመጨረሻው ስንኝ የመጨረሻው ቃል እንዴት ይነበባል?

A. ላልቶ B. ጠብቆ C .ሰልቶ D. ረግቶ

60) በቀረበው ግጥም ውስጥ ስለሚታየው ምጣኔ ምን ማለት ይቻላል?

A. የግጥሙ ሐረጋትና ስንኞች እኩል የሆነ ምጣኔ አላቸው።

B. የግጥሙ ሐረጋትና ስንኞች ምጣኔ እኩል አይደለም።

C. ግጥሙ በሐረጋት ና በስንኞች ምጣኔ አይለካም።

D. የግጥሙ ምጣኔ ናምት የተስተካከለ ለባለመሆኑ ዜማ የለውም።